
# ምዕራፍ ስምንት

## ድህነት




### ከምዕራፍ የሚጠበቁ ውጤቶች


ከዚህ ምዕራፍ በኋላ ተማሪዎች፣

* ስለ ድህነት ምንነት በኢምቋ ትገልጻላችሁ፤
* ድህነት የሚያስከትላቸውን ማኅበራዊ፣ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ቀውሶችን ትዘረዝራላችሁ፤ የድህነት መንስኤዎችን ትለያላችሁ፤
* ከድህነት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን የኢምቋ ምልክቶች ትተነትናላችሁ፤
* የፊትአገላለጽና የአካል እንቅስቃሴ የሚያስከትሉትን የትርጉም ልዩነት ትተነትናላችሁ።

## ቁልፍ ምልክቶች



ድህነት




ሀብት




አስከፊ ድህነት



ቦሊቪያ




ማህበራዊ ቀውሶች




ጦም ማደር




ሶማሊያ




ጊንጥ




መነደፍ




ወባ




ሩዋንዳ




ሞዛምቢክ



ዘይቤ



አገም ጠቀም




ዝርው ዘይቤ




ትሁታዊ ዘይቤ




አሽሙር ዘይቤ




አያዎ ዘይቤ



ሰውኛ ዘይቤ




ገላጭ ዘይቤ



ግነት ዘይቤ



ተነጻጻሪ ዘይቤ



ተለዋጭ ዘይቤ

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### መመልከትና መግለጽ

ከዚህ በታች የቀረበውን ሥዕልተመልክታችሁ፣ከሥዕሉበታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በኢምቋ መልሱ።







1. ከሥዕሉ የተረዳችሁትን ለክፍል ተማሪዎች በኢምቋ አቅርቡ::
2. የድህነት መንስኤ ምንድን ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?
3. ከድህነት ሕይወት ለመውጣትምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?

## ክፍለ ትምህርት ሁለት

### አንብቦ መረዳት

ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ በአንቀጽ ተከፋፍላችሁ ካነበባችሁ በኋላ የአንቀጾችን ፍሬ ሐሳብ ለክፍል ተማሪዎች በኢምቋ አቅርቡ::

#### አስከፊ ድህነት ሲባል ምን ማለት ነው?

ድህነት አሻሚ የሆነ ቃል በመሆኑ፣ አንድ ወጥ ትርጉም መስጠት አዳጋች ነው:: በአንዳንድ ሀገራት በቀን ከአምስት የአሜሪካ ዶላር በታች ገቢ ያላቸው ሰዎች በድህነት ውስጥ እንደሚኖሩ ተደርገው ይታሰባሉ:: በአንዳንድ ሀገራት ደግሞ ልብስና ምግብ ሳይቸግራቸው መጠለያ የሌላቸው ሰዎች በድህነት ይፈረጃሉ:: በአስከፊ ድህነት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ደግሞ የዕለት ጉርስ፣ የዓመት ልብስ፣ መጠለያ፣ የመጠጥ ውኃ፣ የትምህርት ዕድልና የህክምና አገልግሎት ማግኘት የማይችሉ ሰዎች ናቸው:: አስከፊ ድህነት ለሕይወት አስጊነው:: በአስከፊ ድህነት ውስጥ መኖር የእርስ በርስ ጦርነት፣ ስርቆት፣ አካል ጉዳተኝነት፣ ስደት፣ ተላላፊ በሽታ፣ ሙሰኝነት፣ ዘረኝነት ወዘተ፣ ሊያስከትል እንደሚችል ይታመናል::

በአሁኑ ጊዜ አንድ ቢሊዮን የሚያህሉ ሰዎች እንዲህ ባለ ድህነት ውስጥ ይኖራሉ:: ይህ ቁጥር ከአፍሪካ ሕዝብ ብዛት ጋር እኩል ነው:: ያም ሆኖ በምዕራብ አውሮፓና በሰሜን አሜሪካ የሚኖሩ አብዛኞቹ ሰዎች በአስከፊ ድህነት ውስጥ መኖር ሲባል ምን ማለት እንደሆነ አያውቁም:: እስቲ እንዲህ ባለ ድህነት ውስጥ የሚኖሩ የአራት ቤተሰቦችን ሕይወት እንመልከት::

አምባሩ ሺማ ባለትዳርና የአምስት ልጆች አባት ነው:: ነዋሪነቱ አፍሪካ ውስጥ በምትገኘው በሩዋንዳ

ነው። ስድስተኛ ልጁ በወባ በሽታ ሞቶበታል። እንዲህ በማለት ተናግሯል፣ "አባቴ መሬቱን፣ እኔን ጨምሮ ለስድስት ልጆቹ ማከፋፈል ነበረበት። የእኔ ድርሻ በጣም ትንሽ ስለነበር ቤተሰቤን ይዤ ከተማ ገብቼ መኖር ግድ ሆነብኝ። እኔና ባለቤቴ ድንጋይና አሸዋ በመሸከም ቤተሰባችንን እናስተዳድራለን። ቤታችን መስኮት የለውም። ውኃ የምንቀዳው ከቤታችን ራቅ ብሎ ከሚገኝ ጉድጓድ ነው። ብዙውን ጊዜየምንመገበው በቀን አንዴ ሲሆን፣ ሥራ ከሌለ ግን ጦማችንን እናድራለን። የሚላስ የሚቀመስ በሌለበት ቀን ልጆቹ ርቧቸው ሲያለቅሱ ማየት ስለማያስችለኝ ከቤት ወጥቼ እግሬ ወደ መራኝ እሄዳለሁ።"

ቪክቶርና ካርመን የሚተዳደሩት ጫማ በማደስ ነው። እነዚህ ባልና ሚስት ከአምስት ልጆቻቸው ጋር የሚኖሩት ቦሊቪያ ውስጥ በሚገኝ የገጠር መንደር ነው። የተከራዩት አንድ ክፍል ቤት ጣራው የሚያፈስ ከመሆኑም በላይ መብራት የለውም። ትምህርት ቤቱ በተማሪዎች የተጨናነቀ ከመሆኑ የተነሳ፣ ቪክቶር ልጁ ከትምህርት ገበታ ላይ እንዳትቀር ዴስክ መሥራት ግድ ሆኖበታል። ባልና ሚስቱ ምግብ ለማብሰልና የመጠጥ ውኃ ለማፍላት የሚያስፈልጋቸውን ማገዶ ለመልቀም አሥር ኪሎሜትር ያህል ርቀት በእግር መጓዝ አለባቸው። ካርመን እንዲህ ብላለች፣ "መጸዳጃ ቤት የለንም። ስለዚህ ወደ ወንዙ መውረድ ይኖርብናል፤ ሰዎችም ገላቸውን የሚታጠቡትና ቆሻሻ የሚጥሉት ከዚህ ወንዝ ውስጥ ነው። በዚህ የተነሳ ልጆቹ ብዙ ጊዜ ይታመማሉ።"

ፍራንሲስኮና ኤሊዲያ የሚኖሩት ሞዛምቢክ ውስጥ በሚገኝ አንድ ገጠራማ አካባቢ ነው። ከአምስት ልጆቻቸው ውስጥ አንዱ ወባ ይዞት ስለነበር፣ ተኝቶ ለመታከም የሄደበት ሆስፒታል ሳይቀበለው በመቅረቱ ሞተ። ባልና ሚስቱ ባሎቻቸው አነስተኛ መሬት ላይ ሩዝና ስኳርድንች ያመርታሉ፤ ሆኖም ይህ የሚያቆያቸው ለሦስት ወር ያህል ብቻ ነው። ፍራንሲስኮ እንዲህ ይላል፦ "አንዳንድ ጊዜ ዝናብ ሳይጥል ይቀራል ወይም ሌቦች ምርታችንን ከማሳው ላይ ይሰርቁብናል፤ ስለዚህ ትንሽ ገንዘብ ለማግኘት ቀርከሃ እሸጣለሁ። በተጨማሪም በእግር ሁለት ሰዓት ከሚያስኬድ ጫካ ለማገዶ የሚሆን እንጨት እንቆርጣለን። እኔና ባለቤቴ እያንዳንዳችን አንድ አንድ ሸክም ይዘን በመምጣት አንዱን ለሳምንት ያህል ምግብ ለማብሰልእንጠቀምበታለን፤ ሌላውን ደግሞ እንሸጠዋለን።"

ፋርሃንና ሶፍያ ይኖሩ የነበረው ሶማሊያ ውስጥ በምትገኝ ዘወትር በጦርነት በምትታመስ ከሞቃዲሾ ሰማንያ ኪሎሚትር ርቀት ላይ በምትገኝ የገጠር መንደር ነው። ፋርሃንና ባለቤቱ በአካባቢው የሚደረገው ጦርነትና ሽብር ተረጋግተው ኑሮአቸውን ለመምራት ስላላስቻላቸው ያደጉበትን ሥፍራ ለቀው ለስደት ተዳረጉ። ፋርሃን የስደት ቆይታውን ሲያስታውስ እንዲህ ይላል። "ከባለቤቴ ጋር ካደግንበት ሥፍራ ተነስተን የሊብያ በረሃን አቋርጠን ስንጓዝ የደረሰብን መከራ በፊልም የሚታይ እንጂ በእውኑ ዓለም ያለ ክስተት ነው ብሎ ለመቀበል ያስቸግራል። የውኃ ጥሙ ጉሮሮ ይሰነጥቃል። አዘዋዋሪዎች እኔንና ባለቤቴን ለያይተው በመውሰድ ባለቤቴን ደፍረዋታል፣ ሁለት ጊዜ እግሬን በጊንጥ ተነድፌያለው፣ በሊብያ በረሃ ያለው ማዕበል አንድ ጊዜ ተነስቶ አሸዋ ውስጥ ቀብሮን ከሞት ጋር ትንቅንቅ አድርገን ለጥቂት ነው የተረፍነው። ይህን ሁሉ ካለፍን በኋላ የባሕር ላይ ጉዞው በትንሽ ጀልባ ብዙ ሆነን ተጠቅጥቀን ስንጓዝ ማዕበልና አሳነባሪ ተፈታትነውናል። የሰዎች በድን እንደ ቆሻሻ ባሕር ውስጥ ሲጣል ደጋግመን ተመልክተናል። ይህን ሁሉ መከራ አልፈን ጣልያን ብንገባም ባለቤቴ ብዙም አልቆየችም፤ በሞት ተለይታኛለች።" ይላል።

ከሰባት ሰዎች መካከል አንዱ ከአምባሩ ሺማ፣ ከቪክቶር፣ ከፍራንሲስኮና ከፋርሃን ጋር በሚመሳሰል ሁኔታ ሲኖር በቢሊዮን የሚቆጠሩ በሰሜን አሜሪካ፣ በአውስትራሊያና በምዕራብ አውሮፓ የሚኖሩ ሰዎች ግን የተንደላቀቀ ሕይወት ይመራሉ። ብዙዎች በዓለም ላይ የሚታየው ይህ ሁኔታ ግራ የሚያጋባቸው

ከመሆኑም በላይ፣ ፍትሕ እንዳልሆነም ይሰማቸዋል፡፡ እንዲያውም አንዳንድ በጎ አድራጊ ግለሰቦችና ማኅበራት ይህን ያልተመጣጠነ ሁኔታ ለማስተካከል የተለያዩ ሙከራዎችን እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

*(አሹ፣ 2009፣ ድረገጽ ላይ ከለጠፈው ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡)*

## መልመጃ አንድ

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎችበምንባቡ መሠረት በኢምቋ መልሱ፡፡

1. ድህነት ማለት ምን ማለት ነው?
2. በአስከፊ ድህነት ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮች ምን-ምን ናቸው?
3. ፋርሃንና ሶፍያ ለስደት የተዳረጉበት ምክንያት ምንድን ነው?
4. በአሁኑ ጊዜ ምን ያህል ሰዎች በአስከፊ ድህነት ውስጥ ይኖራሉ?
5. በምንባቡ ውስጥ የቀረቡት ባለታሪኮች በአስከፊ ድህነት ውስጥ ሊኖሩ የቻሉባቸው ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

## መልመጃ ሁለት

የሚከተሉትን በተመሳሳይ ምልክት የሚገለጹ ቃላትን ካዛመዳችሁ በኋላ፣ ለመምህራችሁ በኢምቁ አሳዩ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ሌብነት | ሀ.ሽንት ቤት |
| 2. በሽታ | ለ. መኖሪያ ቤት |
| 3. መጠለያ | ሐ. ምግብ ሳይበሉ መተኛት |
| 4. ጦም ማደር | መ.ስርቆት |
| 5. መጸዳጃ ቤት | ሠ. መጥፎ |
| 6. አስከፊ | ረ.ሕመም |

## መልመጃ ሦስት

በቡድን ሆናችሁ ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች ዙሪያከተወያያችሁ በኋላ፣ የውይይታችሁን ውጤት በቡድን ተወካዮቻችሁ አማካይነት ለክፍል ተማሪዎች በኢምቁ አቅርቡ።

1. ብዙ ልጆችን መውለድ ለድህነት መንስኤ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?
2. አንዳንድ ግለሰቦችና ድርጅቶች በበጎ አድራጎት ተግባራት የሚሳተፉት ለምንድን ነው?
3. በበጎ አድራጎት ተግባራት ዝርዝር ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ተግባራት ምን-ምን ናቸው?
4. በመንገድ ላይና በአምልኮ ቦታዎች የሚለምኑ ሰዎችን መርዳት ድህነትን ያስወግዳል ወይስ ያስፋፋል? ለምን?

5. በዓለም ላይ የሚኖሩ ሰዎች በእኩልነት ጤናማ፣ የተረጋጋና ሰላማዊ ኑሮ እንዲኖሩ ምን መደረግ አለበት?

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## ዘይቤያዊ ምልክቶችን መግለጽ

ከዚህ በታች የቀረቡትንየዘይቤ ዓይነቶችን በአንቀጽ ተከፋፍላችሁ ካነበባችሁ በኋላ፣ የአንቀጾችን ፍሬ ሐሳብ ለክፍል ተማሪዎች በኢምቋ አቅርቡ።

### የዘይቤያዊ ምልክቶች ምንነትና አጠቃቀም

የማንኛውም ቋንቋ ተናጋሪዎች ቋንቋቸውን ለማጎልበት እንዲሁም ንግግራቸውን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ አውቀውም ይሁን ሳያውቁ አንድን ነገር ከሌላው ጋር ያመሳስላሉ፣ ያዛምዳሉ፣ ያወዳድራሉ፣ እንዲሁም የአንዱን ነገር ጠባይ፣ ድርጊት፣ ሁኔታ፣ ወዘተ ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል በመውሰድ ሊገለጽ ለተፈለገው ነገር ያጎናጽፋሉ። በዚህ ሁኔታ ዘይቤያዊ አነጋገር ይፈጠራል።

ምልክት ቋንቋ መስማት በተሳናቸው ዘንድ ዋና መግባቢያና ጀሮ ሰም የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችም በስፋት እየተማሩትና እየተግባቡበት ያለ ቋንቋ ነው። በመሆኑም በምልክት ቋንቋ የሚግባቡ የኅብረተሰብ ክፍሎች ሃሳባቸውን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ፣ ለማነጻጸር፣ በተለዋጭ ለማቅረብ ወዘተ ዘይቤያዊ ምልክቶችን (Figurative Signs) ይጠቀማሉ። ዘይቤ የሙያ ቃል ነው። ዘይቤአዊ ምልክቶች የሚለውን እንዲተካ የተደረገው የእንግሊዝኛውን Figurative Signs ነው።

ዘይቤያዊ ምልክቶች የምንላቸው ለተከታዩ ቅርበት ባላቸው ስሜትንና ኃይልን በተላበሱ ምልክቶች፣ በንጽጽር፣ በተለዋጭ፣ በግነት፣ ወዘተ፣ መልዕክት ለማሳተላለፍ ጥቅም ላይ የሚውሉ ምልክቶች ናቸው። ይህም ማለት ድብቅ ወይም ግልጽ ያልሆነ ሐሳብን ግልጽና ብሩህ አድርጎ የማቅረቢያ መንገድ ነው። የዘይቤያዊ ምልክትዓይነቶች ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታቸዋለን።

#### ሀ. ዝርው ዘይቤ

ዝርው ዘይቤ የምንለው ምንም ቅጥል የሌለው፣ ከምንም ነገር ጋር በንጽጽር ያልቀረበ፣ ሊገለጽ የተፈለገውን ሐሳብ የማያንኳስስ ወይም የማያጋንን የዘይቤ ዓይነት ነው። ይህም ማለት ዝርው ዘይቤ የዘይቤዎች ሁሉ መነሻና መድረሻ ነው።

በዝርው ዘይቤ ምሳሌዎች

ሰፊ

ጠባብ

ጥቁር

ነጭ

ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ዝርው ዘይቤ የዘይቤዎች ሁሉ መነሻ ነው ብለናል በመሆኑም በኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ ሌጣ ዘይቤ የምናስተምረው ለምልክት ቋንቋ ጀማሪዎች ነው:: ጀማሪ የኢምቋ አጥኚዎች ስለ ቋንቋው መሠረታዊ እውቀት ሳይኖራቸው አንዱን ከሌላው ጋር ሊያነጻጽሩ፣ የአንዱን ባህሪ ወይም ድርጊት ለሌላው ሊያላብሱ፣ ወይም በግነትና በኩሸት ሊገልጹ አይችሉም:: በመሆኑም የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ ተማሪዎች በቅድሚያ ዝርው ዘይቤ በሚገባ ሊማሩ ያስፈልጋል:: ከዚህ በኃላ ነው ነገሮችን በንጽጽር፣ በግነት፣ በኩሸት፣ ወዘተ ሊገልጹ የሚችሉት::

## ለ. ትሑታዊ ወይም አላዝቤ ዘይቤ

ይህ ዘይቤ የአነጋገር ትሕትናን ለመግለጽ የሚያገለግል ነው:: ለንግግር የሚከብደውንና ለጆሮ የማይጥመውን ሐሳብ በሌላ አገላለጽ አለዝቦ ወይም ንዴት፣ ብስጭት፣ ቁጣ፣ ድንጋጤ ወዘተ ሊያስከትሉ ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ ሐሳቦችን አለዝቦ/ በትሑታዊ አገላለጽ በመግለጽ አድማጩን ከንዴት ከብስጭት፣ ከድንጋጤ፣ ከቁጣ የምንታደግበት /ስሜቱን የምናለዝብበት የአገላለጽ መንገድ ነው::

ይህ የዘይቤ አይነት ነገሮችን ዘለዝቦ ወይም በትሑታዊ አገላለጽ የሚያቀርብ በመሆኑ በኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ እንዴት መግለጽ እንዳለብን ጠንቅቀን ካላወቅን አንዳንድ ጊዜ ሊገለጽ የተፈለገውን ሐሳብ ለአድማጩ/ለተቀባዩ በትክክል ሳናስተላልፍ ልንቀር እንችላለን::


ለምሳሌ፣አባትህ *ሞተዋል* ለማለት አባትህ *አርፈዋል* ወይም አባትህ *አልፈዋል* ብለን ብንገልጽ አድማጩ አባቱ ከሥራ፣ ከጉዞ ወዘተ ማረፋቸውን ወይም በየት በኩል እንዳለፉ ወይም ከምን እንዳለፉ እንጂ መሞታቸውን ላይረዳ ይችላል:: ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ በትሑታዊ ወይም በአለዝቤ ዘይቤ የተገለጸው ሐሳብ የተፈለገውን መልዕክት ላያስተላልፍ ይችላል::

በመሆኑም በኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ አንድን ሐሳብ በአለዝቤ/ትሑታዊ/ ዘይቤ ለመግለጽ የፊት አገላለጽ ወሳኙን ሚና ይጫወታል::

ለምሳሌ፣ ባለፈው ዓመት በኤች አይ ቪ/ኤድስ በርካታ ሰዎች *ሞተዋል* ለማለትና የቅርብ ወዳጃችን ለሆነ ሰው የአባቱን/የእናቱን፣ የቅርብ ዘመዱን/*ሞት* የምናረዳበት/ *ሞተዋል* ብለን የምንነግርበት/ መንገድ የተለያየ ነው፤ ለዚህም የተለያየ የፊት አገላለጽ መጠቀም ያስፈልጋል::

## ሐ. አሽሙር/አግቦ

በነገር፣ በተንኮል፣ በአሽሙር ሌሎችን ሰዎች የመንኪያ፣ የመልከፊያ ወይም የመስደቢያ ሥልት ነው:: ይህ የዘይቤ ዓይነት እንደ ሀሜት ይቆጠራል ነገር ግን ከሀሜት የሚለየው የሚታማው ወይም የሚሰደበው ሰው እዚያው በቦታው መኖሩ ነው::



ምሳሌ፣ ሀ፣ ለ፣ እና ሐ፣ የሚባሉ ሦስት ሰዎች አሉ። ሀ እና ለ ይዋደዳሉ ጓደኞሞችም ናቸው፤ ለ እና ሐ እንደዚያው ይዋደዳሉ ጓደኞሞችም ናቸው። ሀ እና ሐ ግን አይግባቡም። ሀ ሐ ን ለመዝለፍ ወይም በነገር ለመተንኮስ ቢፈልግ የሚሳደበው ወይም የሚዘልፈው በቀጥታ ሐ ን ሳይሆን ለ ን ነው። ለ ለምን ተዘለፍኩ ወይም ተሰደብኩ ብሎ አይናደድም ይልቁንም የሚበግነው/የሚናደደው/ ሐ ነው። የዚህ ዓይነት ዘይቤን ነው አሽሙር ወያም አግቦ የምንለው።

በኢምቋ ይህ የዘይቤ ዓይነት በአማርኛ ቋንቋ ካለው አገላለጽ ብዙም የተለየ አይደለም። በአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪው ስድቡን የሚሳደበው ወይም ዝልፊያውን የሚያወርደው በድምጽ ነው። ተሰዳቢው ወይም ተዘላፊው እዚያው ሆኖ ሊሰማው ይችላል። በኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ ግን ሀ የተባለው ግለሰብ ለ ን የሚሰድበው ሐ ን የጎሪጥ እያየ ነው። ሐ የተባለው ግለሰብ እየተሰደበ መሆኑን የሚያውቀው ሀ የተባለውን ግለሰብ የእጅ እንቅስቃሴ ተመልክቶ ሳይሆን ሀ የተባለው ግለሰብ የዐይን እንቅስቃሴ ተመልክቶ ስድቡ ወይም ዝልፊያው ለእሱ መሆኑን በቀላሉ ሊረዳ ይችላል።

በልሳን ቋንቋ የድምጽ ቅላጼ (የድምጽ አወጣጥ) መልዕክቱን ሊቀይር እንደሚችል ሁሉ በምልክት ቋንቋ የፊት አገላለጽ፣ የምላስ አወጣጥ፣ የዐይን በጣም መከፈትና መጥበብ፣ ወዘተ መልዕክቱን የመቀየር ኃይል አላቸው። በመሆኑም በዚህ የዘይቤ ዓይነት መልዕክቱን ወደተፈለገው ለማድረስ የዐይን እንቅስቃሴ ወሳኙን ድርሻ ይይዛል።

### መ. አገም ጠቀም

ጥሩና መጥፎ፣ የምስጋናና የወቀሳ፣ ድክመትና ትንካሬ፣ ተቻችለው የሚመጡበት(የሚነገሩበት) የዘይቤ ዓይነት ነው።

ምሳሌ፣ ጫማሽ ሸፋፋ ነው እንጂ ባተ መልካም ነሽ።

አታፈጥንም እንጂ ጥሩ ትሠራለህ።

ይህ ዘይቤ በኢምቋ አለ ሆነ ምን የለም ሆነ ምን ከሆነ ምን አልሆነም ምን የሚሉትንና የመሳሰሉትን ምልክቶች ችግር ፈጥሮዋል (ወይም ለድክመቱ ምክንያት ነው ብለን ከምናስበው ነገር ወይም ይህ ባይከሰት ኖሮ ብለን) ከምናስበው ነገር ለጥቆ በመጠቀም ሊገለጽ የተፈለገው ነገር ድክመትና ጥንካሬ፣ ወይም ሃሳቡን ለማፍረስና ለማጠናከር የምንጠቀምባቸው በአገም ጠቀም ዘይቤ ዓይነት የሚመደቡ ናቸው።

በዚህ የዘይቤ ዓይነት የፊት እንቅስቃሴ በተለይ የግንባር ከፍና ዝቅ ማለት ወይም የግንባር ቆዳ መሸብሸብና መዘርጋት ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለው። አንድን ሐሳብ ለማፍረስ ወይም ለማጎልበት ወይም አንድን ነገር ለመደገፍ ወይም ለማንኳሰስ የምንጠቀምበት አገላለጽ ቀጥተኛ አይደለም በመሆኑም ሊስተካከል የፈለግነው ነገር አስቀድመን በመግለጽ ነገሩ ከተስተካከለ በኋላ የሚገኘውን ውጤት ቀጥለን እንገልጻለን። በሌላ በኩል ይህ ባይኖር ኖሮ እንዲህ ይሆን ነበር እንደምንለው ዓይነት ነው።

ምሳሌ ቦርጭ የለም ሆነ ምን አቋም ቆንጆ (ቦርጭ ባይኖርበት አቋሙ ያምራል ለማለት)

ምናልባት ማንበብ ችሎታ ኖረ ምን? ጭንቅላት (አእምሮ) በላይ (ማንበብ

አይችልም እንጂ ጥሩ ጭንቅላት/የአስተሳሰብ ችሎታ/ አለው ለማለት)

ሠ. ንጽጽር

ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ነገሮች በመካከላቸው ያለውን ተመሳሳይነት አንዱን በሌላው አጉልቶ በማውጣት ወይም አንዱን ከሌላው ጋር በማነጻጸር በመካከላቸው ያለውን ተመሳሳይነት የምንገልጽበት የዜቤ ዓይነት ነው፡፡

ምሳሌ  እርኩስ እንደ እባብ

የዋህ እንደ እርግብ

ዛፉ ሰማዩን ቀድዶ የገባ ይመስላል

በኢምቋ ሊገለጽ የተፈለገው ነገር ገላጩን እንደሚመስል ወይም አነጻጻሪው ተነጻጻሪውን እንደሚያክል ለመግለጽ ከአነጻጻሪውና ከተነጻጻሪው ምልክት ለጥቆ ተመሳሳይ የሚለውን ምልክት እናሳያለን፡፡

ምሳሌ  ከበደ ቁመት አባት ቁመት ተመሳሳይ/እኩል/ (ከበደና አባቱ በቁመት እኩል ናቸው ለማለት)

አልማዝ መልክ እናቷ መልክ ተመሳሳይ /perfect/ (አልማዝ ቁርጥ እናቷን

ትመስላለች ለማለት)

እሱና እባብ ተንኮል ተመሳሳይ፡፡ (እሱ እንደ እባብ ተንኮለኛ ነው ለማለት)

## መልመጃ አምስት

ከላይ የቀረበውን ዘይቤያዊ ምልክቶች አንብባችሁ፣ ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልሶች በደብተራችሁ ሠርታችሁ ለመምህራችሁ በምልክት ቋንቋ ግለጹ፡፡

1. አምስት የዝርው ዘይያዊ ምልክቶች በደብተራችሁ ጽፋችሁ በኢምቋ እንዴት እንደሚገለጹ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡
2. አምስት አላዝቤያዊ ምልክቶች በኢምቋ እንዴት እንደሚገለጹ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡
3. አምስት የአሽሙር ዘይቤያዊ ምልክቶችን ሠርታችሁ በኢምቋ እንዴት እንደሚገለጹ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡
4. አምስት የአገም ጠቀም ምልክቶችን በደብተራችሁ ጽፋችሁ በኢምቋ እንዴት እንደሚገለጹ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡
5. አምስት ንጽጽር የሚገልጹ ምልክቶችን በደብተራችሁ ጽፋችሁ በኢምቋ እንዴት እንደሚገለጹ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

**ከዚህ በላይ የቀረቡትን የኢምቋ ዘይቤዎች ምሳሌ በማድረግ ለሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ በደብተራችሁ ከጻፋችሁ በኋላ በኢምቋ ለመምህራችሁ ግለጹ።**

1. አሽሙር ዘይቤ
2. ገላጭ ዘይቤ
3. ተነጻጻሪ ዘይቤ
4. ግነት ዘይቤ